# በኢትዮጵያ ላይ የፋሺስት ኢጣልያ ወረራና የፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ አቋም

ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤል*

## *Abstract*

*It is well established that the 1935 Italian invasion of Ethiopia was primarily aimed to take a revenge of the humiliation she experienced during the battle of Adowa, and a number of studies have chronicled the barbaric cruelty inflected by well-armed Italian army on ill equipped and untrained Ethiopian fighters. In spite of that, most research reports fail to reflect the historical facts regarding the attitude and the position of Pope Pius XI and the Vatican towards the Italo-Ethiopian conflict and the subsequent massacres. The present study seeks to examine real position and attitude of the Pope towards the Italian invasion and massacre of its people for five years. To that end, many archives and historical documents have been used to collect data. A closer examination of archives reveal that Pope Pius XI has directly and indirectly supported Italian invasion of Ethiopia and her atrocities, and he never spoke out against what was clearly an unjust war. On June15, 1935, Pope Pius XI granted an audience to 7,000 veterans and celebrated a mass in their presence in an encouragement to the soldiers for massacre and an ideological support to Fascist Italy. On August 27, 1935 Pope Pius XI also granted an audience to an international congress of Catholic nurses at Castel Grandolfo and addressed them making special reference to the Italo-Ethiopian war as a distinct tribute of sympathy for Italy's desire of colonization. In his expression "it is said in Italy that the war would be a just war because of the expansion of a population" the Pope clearly reflected Mussolini's point of view and argument for his war against Ethiopia, and he seems to have believed that the war was just and, therefore, entreated only for "limits and moderation." The Pope publicly expressed his joy at the victory of the Italian army over Ethiopia and described it as a "happy triumph."Encouraged by the Pop's position, most of the Catholic Bishops, Clergies and the Press strongly condemned the League of Nations for imposing sanctions against Italy and labeled the move as immoral. Members of the Italian hierarchy and the clergy apparently took a clear position in favor of the Italian war against Ethiopia and gave every possible support moral and material, to the Fascist leaders and army in their adventure of invading Ethiopia. The pope did not check and instruct his Italian Bishops to abstain from such warlike and ultrapatriotic pronouncements. The absence of such intervention by the Pope would only mean that he silently approved the behavior of the Italian hierarchy. The Pope's indirect support of the war is revealed by his silence and failure to condemn the many atrocities and massacres inflicted by fascist Italy including: the execution of Abune Petros, Abune Mikael, the monks of Debre Libanos monastery, and the atrocity that took place at Zuquala Monastery by the Fascists. He had turned a deaf ear to the use of poison gas and the deliberate bombardment of the Red Cross ambulance units by the Italian army in Ethiopia in breaches of the International Covenant to which Italy itself subscribed. Hence, it is recommended that Vatican has to ask Ethiopian peoples a pardon for supporting Mussolini's aggression against Ethiopia. Vatican and Italians must return all the precious and timeless manuscripts looted from many Monasteries of Ethiopia. The Italian Government should also proportionally compensate Ethiopia for the war time damages.*

*ቀሲስ ዶ/ር ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በዋና ዲንነትና በመምህርነት፣ በአዲስ አበባ ፕሬስ በአርታዒነት፣ በአፍሪካ የተባበሩት ዐለም ዐቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የትርጉም ባለሙያና አማካሪ ኾነው አገልግለዋል። በአኹኑ ወቅት በግል የጥናትና ምርምር ሥራዎችን እየሠሩ ይገኛሉ።

## ፩. መግቢያ

የኢጣልያ አምባገነን መሪ የነበረው ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን ለመውረር ከኢጣልያን የሃይማኖትና የሲቪል ሕዝብ የሞራልና ቁሳቁስ ድጋፍ ለማግኘት ብዙ ጥረት አደረገ፡፡ ከዐርባ ዐመታት በፊት በዐድዋ የደረሰባቸውን ከባድ ሽንፈት ለመበቀል ይፈልጉ ከነበሩት ኢጣልያውያን የሚያስፈልገውን ድጋፍ ኹሉ ለማግኘት ቻለ፡፡ ስለዚህም በታላቅ እብሪትና የዐለም መንግሥታትን ማኅበር ደንብ በመጣስ ኢትዮጵያን ለመውረርና ቅኝ ግዛት ለማድረግ ተነሣ፡፡ ለዕቅዱ ማሳኪያ የመጀመሪያ ምዕራፍ ያደረገውም ኅዳር ፳፮፣ ፲፱፻፳፯ ዐ.ም. ወልወል ላይ በነበሩት የኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ጥቃት ሰንዝሮ ጉዳት ማድረስን ነበር፡፡ ኢትዮጵያን ጠቅልሎ ለመያዝ ዝግጅት ያደረገው የኢጣልያ ጦር መስከረም ፳፪፣ ፲፱፻፳፰ ዐ.ም. መረብን ተሻግሮ በሦስት አቅጣጫ በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ከፈተ፡፡ የኢትዮጵያ ጦር የኢጣልያንን ወረራ ለመመከትና ለማጥቃት እርምጃ መውሰድ የጀመረው ዘግይቶ በጥር ወር ፲፱፻፳፰ ዐ.ም. ነበር፡፡ ቅንጅት ያልነበረው የኢትዮጵያ ጦር የረጅም ጊዜ ዝግጅት በነበረው የኢጣልያ በጦር መሣሪያና በሰው ኃይል ተበልጦ በቀላሉ ተሸነፈ፡፡[1] የኢጣልያ ጦርም ኢትዮጵያን ወርሮ በቆየባቸው አምስት ዐመታት ብዙ የግፍ ተግባሮችን ፈጸመ፡፡

የኢጣልያ ጦር በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመውን ወረራ ርእሰ ጉዳያቸው ያደረጉ በርካታ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ ጥናቶቹ፣ በጊዜው የነበረውን የኃይል አሰላለፍ የኢትዮጵያውያን ዐርበኞችን ተጋድሎ፣ የኢጣልያ ቅኝ ገዢ ጦር በኢትዮጵያውያን ላይ የፈጸመውን ግፍ፣ ወዘተረፈ ዘግበዋል፡፡ ይኹን እንጂ፣ የኢጣልያ ወራሪ ጦር በኢትዮጵያ ላይ በከፈተው ጥቃት የሮሙ ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ አቋምን በተመለከተ የተዘገበው ትክክለኛውን የታሪክ እውነታ አያስረዳም፡፡ ከኹሉም በላይ፣ "የመንበረ ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን መሪ ፒዮስ ፲፩ኛ ኢትዮጵያ በፋሽስት መንግሥት በተጠቃችበት ዘመን የሙሶሊኒ ተባባሪ አልነበረም፡፡ ይልቁንም ቅዱስ ፓፓው ለኢትዮጵያ አዛኝና የተለየ አስተያየት የነበራቸው መንፈሳዊ አባት ነበሩ፤"[2] በማለት የተዘገበው የመረጃ ክፍተትና የመረጃ አተረጓጎም ስሕተት እንዳለበት እንገነዘባለን፡፡ ክፍተቱም ይኽን ጥናት ለማቅረብ ምክንያት ኾኗል፡፡

በመኾኑም፣ የዚኽ ጥናት ዐቢይ ዐላማ ከ፲፱፻፳፰ ዐ.ም. እስከ ፲፱፻፴፫ ዐ.ም. ኢጣልያ ኢትዮጵያን ወርራ በቆየችበት ጊዜ ስለ ፈጸመቻቸው የግፍ ተግባሮች የፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ አቋም ምን እንደ ነበር መመርመር ነው፡፡

---

[1]ባሕሩ ዘውዴ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ፲፰፻፵፯ እስከ ፲፱፻፹፫፤ ዐዲስ አበባ፣ ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ ፲፱፻፺፱፣ ገጽ ፻፰፪፡፡

[2]ዘውዴ ረታ፤ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ፩ኛ መጽሐፍ ፲፱፻፳፫-፲፱፻፵፰፤ ኢ.ኤ.አ. ፲፱፻፴-፲፱፻፶፭፤ ፳፻፫፣ ገጽ ፫፻፲፬፡፡

ይኸንን መሠረት ያደረጉ ዝርዝር ዐላማዎችም፡- ፩ኛ. ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በግፍ ስትወርር ቫቲካን በፖፑ አማካይነት ምሥጢራዊ የኾነ የሞራል ድጋፍ ለኢጣልያ መስጠቷን፣ ፪ኛ. የኢጣልያ ወታደሮች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በተለይ በየካቲት ፲፪ እና ፲፫ ቀናት፣ ፲፱፻፳፱ ዐ.ም. እጅግ የሚያሰቅቅ የጭካኔ ጭፍጨፋ በማድረጋቸው ዐለሙ ኹሉ ሲጮህ ቫቲካን ምንም ድምፅ አለማሰማቷን፣ ፫ኛ. የፋሺስቱ የኢጣልያ ወታደሮች የመርዝ ጋዝ እየረጩ ድልን ባገኙ ጊዜ ፖፑ ይኸን ድል የሚያስደስት ድል ብለው ማወደሳቸውን፣ ፬ኛ. የፋሺስቱ ጭፍሮች ከ፳፻ የሚበልጡ የኢትየጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናትንና ገዳማትን ሲያቃጥሉ፣ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ መነኰሳትንና ካህናትን እንዲሁም ጳጳሳትን በግፍ ሲገድሉ ቫቲካን ዝም ብላ መመልከቷን ማስረዳት የሚሉት ናቸው፡፡

ጥናቱም፣ የፋሺስቱ ኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት የሮሙ ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ትክክለኛ አቋም ምን እንደ ነበር በማስረዳት በዚኽ በኩል የነበረውን የታሪክ ክፍተት ይሞላል፡፡ በተጨማሪም በወረራ ወቅት ስለ ተፈጸመው የግፍ ተግባርና ስለ ተዘረፈው በርካታ የሀገር ቅርስ ዛሬ ምን ማደረግ እንደሚገባ ለሚመለከታቸው ኢትዮጵያውያን ኹሉ ያሳስባል፡፡

የዚኽ ጥናት መረጃዎች በዋናነት የተሰበሰቡት በተለያዩ ሀገሮች ከሚገኙ አብያተ መዛግብት ከምችቶች ነው፡፡ በተለይም የእንግሊዝ ሕዝብ ማኅደር መ/ቤት (The British Public Record Office)፣ በኤደንብራህ ሀውስ የሚገኘው የእንግሊዝ መማክርት አብያተ ክርስቲያናት የቀድሞ ዐለም ዐቀፍ ወንጌል ሰባኪ ምክር ቤት (The former International Missionary Council kept at the British Council of Churches at Edinbrugh House)፣ ከላምበት ፓላስ ቤተ መጻሕፍት (The Lambeth Palace Library) እና በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ከሚገኘው ቸርች ሚኒስትሪ ቦድሊያን ቤተ መጻሕፍት (The Church Ministry to Jews deposited at the Bodleian Library, Oxford University)፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ ሥር የሚገኘው የኢየሩሳሌም ገዳምና ትምህርት ሚኒስቴር ሥር ከሚገኙ አብያተ መዛግብት ጠቃሚ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከዚኽም በላይ ከመጻሕፍት፣ በዐማርኛ ከታተሙ ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና መጻሕፍት እንዲሁም ከግለሰቦች ለጥናቱ የሚረዱ መረጃዎችን መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ከተጠቀሱት ምንጮች የተሰበሰቡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ስትወርር ቫቲካን በተለይም የፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ አቅዋም ምን እንደ ነበር ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## ፪. የቫቲካን አቋም

ቫቲካን በኢትዮ-ኢጣልያን ጠብና ግጭት ወቅት ኹሉ አጠራጣሪ ወይም አሻሚ አቋም ነበር የወሰደችው፡፡ ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ በኢትዮ-ኢጣልያ ጠብ ጊዜያት ይናገሯቸው

በነበሩት የፖሊቲካ ንግግሮች ኹሉ የገለልተኝነት መንፈስ ለማሳየት ሞክረው ነበር። ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን ለመውጋት ዝግጅት ሲያደርግና የመንግሥታቱ ማኅበር ለችግሩ የበኩሉን ሰላማዊ መፍትሔ ለማግኘት በሚፈልግበት ጊዜ ኹሉ ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ዝም ነው ያሉት።[3] በተለያዩ ሀገሮች የነበሩ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ስለ ችግሩ በብዙ ሲጨነቁና የመንግሥታቱም ማኅበር የሚችለውን ኹሉ እንዲያደርግና ሰላሙን እንዲያወርድ ሲማጸኑ፣ ፖፑ የመንግሥታቱ ማኅበር ጠቡንና በኹለቱ ጠበኛ ሀገራት መካከል ሊከሰት የሚችለውን ጦርነት ለማቆም ያደርግ የነበረውን ሙከራ በመደገፍ ምንም አልተናገሩም፤ ወይም ራሳቸውም ቢኾን በኹለቱ ሀገራት መካከል ሰላምን ለማምጣት ምንም ሐሳብ አላቀረቡም።[4]

ባየር (እ.ኤ.አ. ፲፱፻፷፯ ዐ.ም.) የተባለው ሊቅ የቫቲካንን አቅዋም በመተቸት ከዚህ የሚከተለውን ይጽፋል፡-

> ቅዱሱ መንበር (ቫቲካን) ዋናውን ወራሪ አላስጠነቀቁም (አልመከሩም) ወይም አላወገዙትም ወይም ተጠቂውን አካል አላጽናኑም። የዐለም ዐቀፍ ሕግንና የተደረገውንም የማስታረቅ ጥረት አልደገፉም።[5] … ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ከእርሳቸው በፊት እንደነበሩት እንደ ፖፕ በኔዲክት ፲፭ኛ[6] የሥነ ምግባሩና የሕግ መሠረቱ ከክርስቲያን ሃይማኖት ጋር ተመሳሳይ የኾነውን የመንግሥታቱን ማኅበር ጥረት ፈጽሞ አልደገፉም ወይም አላበረታቱም።[7]

ብዙ ሰዎች ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ በኾለቱ ለጦርነት በሚፈላለጉ ሀገሮች መካከል ጣልቃ ገብተው ለማስታረቅ ይሞክሩ ይኾናል ብለው በከንቱ ተስፋ አድርገው ነበር። ኹለቱ

[3]Walters, *A History of the League of Nations*, II, 1952, 647-671.

[4]ዋልተርስ ሲጽፉ እንዲህ ብለዋል፡- “እ.ኤ.አ. ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፴፭ ዐ.ም. የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስና የኡፕሳላው ሊቀ ጳጳስ በአንድነት ለመንግሥታቱ ማኅበር ምክር ቤት (council) ሰላምን እንዲያወርዱ አቤቱታ አቅርበዋል። በነሐሴ ወር ደግሞ ዐለም ዐቀፉ የክርስቲያን ጉባኤ (IMC) በላከው መግለጫ የመንግሥታቱ ማኅበር የመላው አብያተ ክርስቲያናት ድጋፍ እንዳለው አረጋግጠ ውለታል፤ ቫቲካን ብቻ ዝም አለች።”

[5]ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ፪፻፹፯።

[6]በመጀመሪያው የዐለም ጦርነት ጊዜ ፖፕ በኔዲክት ፲፭ኛ አንድ ትልቅ የሰላም-አደራዳሪ ሥራ ሠርተዋል። እ.ኤ.አ. ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፲፯ ለልዩ ልዩ መንግሥታት በጻፉት ደብዳቤ ፖፕ በኔዲክት ፲፭ኛ አንድ ደስ የሚያሰኝ የሰላም ዕቅድ አውጥተው ነበር። እሳቸው እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- “መሠረታዊው ነጥብ የሥነ ምግባርን ኃይል በቁስ አካል የጦር መሣሪያ ኃይል ላይ መተካት ነው። ስለዚህ እውነተኛና ለኹሉም የሚኾን ስምምነትና በኹሉም ዘንድ የሚጸና የጦር መሣሪያ ቅነሳ …የማስታረቂያ (የሽምግልና) ተቋም …ማዕቀብ የዐለም ዐቀፍ ሽምግልናን እና ውሳኔውን በማይቀበሉ ላይ ማጽናት ነው።” (See, L. Sturzo, Church and State, II, trans. A. R. Caponiguri, University of Notre Dame Press, 1962, 472-473). እኚህ ሰው የመንግሥታቱ ማኅበር በችግር ላይ በነበረበት ጊዜ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል። PacemDei በተሰኘው ለኹሉ የተጻፈ (circular) ደብዳቤ ላይ የሚከተለውን ዐውጀዋል፡- “በአንድነት ለተሰበሰቡት መንግሥታት በክርስትና ሕግ መሠረትም ለተቋቋመው ድርጅት ቤተ ክርስቲያን ስለ ሰላምና የበጎ አድራጎት ሥራ በሚያደርጉት ኹሉ በእምነት ሙሉና ትክክለኛ ኅብረቷን ትሰጣለች።” Sturzo, Op. Cit., p 475.

[7]Baer, *The Coming of Italian-Ethiopian War*. 1967, pp. 287-288.

ሀገሮች እ.ኤ.አ. በ ፲፱፻፳፰ ዐ.ም. በአደረጉት የወዳጅነት ስምምነት መሠረት ልዩነታቸውን በሽምግልና እንዲጨርሱ ፖፕ በሙሶሊኒ ላይ ተፅዕኖ ያደርጋሉ ተብሎ ታስቦ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ልዩነቱን በሽምግልና ለመጨረስ ዝግጁ ነበረች፡፡[8] ሩም የተባሉ ምሁር ርግጠኛ ኾነው እንዲህ ይላሉ፡- “በመጀመሪያ የፖፑ አንዲት ቃል የሙሶሊኒን የሽፍትነት ወረራ ሊያቆመው ይችል ነበር፡፡ ያች ቃል ግን ከፖፑ አልተነገረችም፡፡”[9]

በዚኽ እጅግ አሳሳቢ በኾነው ጊዜ ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ዝም ለማለታቸው ምክንያት ለመፈለግ ብዙ ሙከራዎች ተደርገዋል፡፡ ያኔ ካርዲናል የነበሩት የዌስት ሚኒስተር ሊቀ ጳጳስ ሄንስሌይ (Hensley) ስለዚኹ ጉዳይ ንግግር ሲያደርጉ እንዲኽ አሉ፡-

ፖፑ ይኽንን ወይም ማንኛውንም ጦርነት ለመከልከል ምን ማድረግ ይችላሉ? እሳቸው አቅም የሌላቸው ሽማግሌ ናቸው፡፡ ራሳቸውንና እጅግ ውድ የኾኑ የቫቲካንን የወግ ዕቃዎች የሚጠብቁ ጥቂት የፖሊስ ኃይል ነው ያላቸው … እጅግ ኃይለኛና ብዙ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የታጠቀውን፣ ኹሉን በቍጥጥሩ ሥር ያደረገውንና ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀ ኃይል ያለውን የጕረቤት ኃይል ለመወንጀል ይችላሉ? አንዳንድ ሰዎች ሊያወግዙት ይችሉ ነበር ይላሉ፡፡ አዎን ይችላሉ! በዚህም ከአምባገነን ጕረቤት ጋር ጦርነት ይግጠሙ! ከዚኽም ሌላ ሰላምን ያደፍርስ ወይም የብዙውን የኢጣልያ ሕዝብ አበሳጭቶ በካህናት ላይ ጦርነትን ይቀስቅስ![10] እንደ እውነቱ ከኾነ ፖፑ “አቅም የሌላቸው ራሳቸውን … የሚጠብቅ ጥቂት የፖሊስ ኃይል ብቻ ያላቸው ናቸው፤” የተባለው ከጉዳዩ ጋር ያልተያያዘ አነጋገር ነው፡፡ ፖፑ በሙሶሊኒ ላይ የወታደር ርዳታ እንዲሰጡ አልተጠየቁም፡፡ ከእሳቸው በእውነቱ የተጠበቀው የሥነ ምግባር አመራርንና የክርስትና ሃይማኖት ምስክርነትን እንዲሰጡና ኢፍትሐዊ ድርጊትን (ኢፍትሐዊ ጦርነትን) እንዲያወግዙ ነበር፡፡

የፖፑን ገለልተኛነት በመተቸት The New Times and Ethiopia News የተባለ ጋዜጣ እንዲኽ ይላል፡- ቫቲካን በአኹኑ ጊዜ አንድ ዐለማዊ ኃይል ነው፡፡ በዚኽም የፖሊቲካ ገለልተኛነት ሊኖረው ይችላል፡፡ ኾኖም የፖፑ ዐለማዊ ኃይል ከሥነ ምግባር ውጭ ሊኾን

[8]*League of Nations Treaty Series*, 1935 p. 94, 1929, pp. 416-423. *The League of Nations, Official Journal*, pp. 270 -274.

[9]Wm. J. W. Rome, (1936). *Ethiopia the Valiant,* London: Marshal, Morgan and Scott Co. td.,72.

[10]ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ ፸፪-፸፫. Toynbee, *Survey of International Affairs, 1935, II, Abyssinia and Italy,* ፶፫-፶፬. ሊቀ ጳጳስ ሄንስሌ በጦርነቱ ወቅት ስለ ሙሶሊኒ እንዲኽ ብለው ተናግረዋል፡ “የፋሺስት ሥርዐት ከወደቀ የእግዚአብሔርም ዐላማ ወደቀ ማለት ነው፡፡” See Edit Moore, *The Vatican in War and Peace,* London: International Publication Co., 1944, p.2. መሪያቸውን በመከተል ሊቀ ጳጳስ ሄንስሊ እንዲኽ አሉ፡- “በእንግሊዝ ሀገር የሮማን ካቶሊክ ቤት ክርስቲያን የኢጣልያንን ጉዳይ ከሚደግፉ ጋር ትተባበራለች፡፡” ይኽንን እነሱ በይፋ አልተናገሩም በድብቅ እንጂ A. J. Barker, *The Civilizing Mission: A History of the Italia.*

አይችልም፡፡ ስለዚኽ ፖፑ የሥነ ምግባር ገለልተኝነት ሊኖራቸው ፈጽሞ አይችሉም ፡፡ የሥነ ምግባርና መመሪያ አደጋ ላይ በኾነ ጊዜ ዓለም ከፖፑ ልዩ የኾነ አመራርን ይጠብቃል፡፡ ይኽ ካልኾነ ግን የፖፑ የፖሊቲካ አቋም ዋጋ የለውም፡፡[11]

ለፖፑ ዝምታና የዐለም ዐቀፍ የሥነ ምግባር ውድቀትን የፈጠረውን የፋሺስትን ወረራ በኢትዮጵያ ላይ ተቀብሎ ዝም ማለት ሌላ ምክንያት የሚሰጡት ለሃምሳ ዐመታት የቆየውን በኢጣልያና በቫቲካን መካከል የነበረውን ጸብ ያቆመውን በፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛና በሙሶሊኒ መካከል የተፈረመውን በ፲፱፻፳፱ ዐ.ም. የተደረገው የላተራን ስምምነት ምክንያት ፖፑ የነበረባቸውን ሓላፊነት ነው፡፡ ይኽ ስምምነት ፖፑ በኹለት ሥልጣናቸው ማለት የዐለም ዐቀፍ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መሪና የነፃይቱ ሀገር የቫቲካን ዐለማዊ መሪነታቸው የተረጋገጠበት ስምምነት ነበር፡፡ ዐለማዊ ባለሥልጣን እንደመኾናቸው መጠን ፖፑ በፖሊቲካ ሥልጣናቸው "በስምምነቱ በዐንቀጽ ፳፬ ቫቲካን ከሌሎች መንግሥታትና ከሚሰበሰቡ ከዐለም ዐቀፍ ስብሰባዎች ጋር ተወዳዳሪዎች ወገኖች ተስማምተው የሰላም ሚስዮኑን እንዲያካፍሉ ፖፑ ካልተጋበዙ በስተቀር ከውድድሩ ውጭ ይሆናሉ፡፡"[12] ይላል፡፡ ኾኖም ፖፑ በዚያው አንቀጽ ፳፬ ላይ "የራሳቸውን የመንፈሳዊና የሞራል ተቃውሚቸውን የማሰማት መብታቸውን አስጠብቀዋል፡፡"[13] ስለዚኽ ፖፑ በዚኽ ዐንቀጽ መሠረት የሞራል ጥያቄን በሚመለከት ድምፃቸውን ለማሰማት ይችሉ ነበር፡፡ ደካማው በኃይለኛው በመጠቃቱ፣ የኢትዮጵያ ጉዳይ የሞራል ጉዳይ ነበር፡፡ ፖፑ ይኽንን ድምፅ ለማሰማት አልፈቀዱም፡፡

ኾኖም ፖፑ የኢጣልያንን ወረራ ለማውገዝ ያልቻሉበት የእሳቸውን እውነተኛ አቋም ይገልጹ የነበሩ ሌሎች ምክንያቶች ነበሯቸው፡፡ እነዚህም፡-
፩ኛ. ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ የፈሩት ኢጣልያ ኢትዮጵያን መውረሯን ቢያወግዙ በኢጣልያና በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መካከል በተለይም በፖፑና በካርዲናሎቹ መካከል፣ በሌላ በኩል ደግሞ እጅግ ሀገር ወዳድ መኾናቸውን ከገለጹት ብዙ በሆኑት በኢጣልያ ካህናት መካከል ጥላቻን ይፈጥራል ብለው ፈርተው ነበር ይባላል፡፡[14]

፪ኛ. ፖፑ ፋሺስቱን ለመደገፍ ያነሣሣቸው ምክንያት በዚያን ጊዜ በኢጣልያ በካህናት ላይ ተነሥቶ በነበረው ከባድ ተቃውሞ (anticlerical movement) ፖፑ እጅግ ታውከው ነበር፡፡ ስለዚኽ የፋሺስትን ንቅናቄ ለማድከም አልፈለጉም፡፡ የፋሺስትን ንቅናቄ ማዳከም የካህናትን ተቃውሞ ማበረታት ነው ተብሎ ይታመን ነበር፡፡ በቫቲካን እንደሚታመነው

[11] *The New Times and Ethiopia News*, January 13, 1936.
[12] Sturzo, *Op. Cit.*, 501-502.
[13] Sturzo, *Op. Cit.*, 501-502. See also Baer, *Op. Cit.*, 283.
[14] *The Manchester Guardian*, February. 24, 1936.

የፋሺስት ንቅናቄ መድከም በልሼቪዝምንና የካህናት ተቃውሞን ያመጣል ተብሎ ይገመት ነበር።[15]

በርግጥ ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ በኢጣልያና በሌሎች ሀገሮች የኮሚኒስት ንቅናቄ መስፋፋቱ ለክርስትና ሃይማኖት በተለይም ለእርሳቸው (ለካቶሊክ) ቤተ ክርስቲያን ጠንቀኛ ስለኾነ በጣም ተጨንቀው ነበር። በእሳቸው አስተሳሰብ "ዲሞክራሲ የኮሚዩኒዝምን ማዕበል ለመቋቋም በጣም ደካማና ያልተያያዘ ኃይል ነው፤" ብለው ያምኑ ነበር። ዳንኤል ቢንቺ እንደሚሉት "ፖፑ የዐምባገነኖች አስተዳደር የኮሚኒስትን ሥርዐት የሚከላከል ነው ብለው አምነዋል።"[16] "ስለዚኽ ፖፑ የቤተ ክርስቲያንን ሰላም ከፋሺስቶች ጋር አንድ አደረጉ፤" ቤር እንዳሉት "ፖፑ ሙሶሊኒ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተነሣ፣ በሊብራሊዝም ያልተሞኘ ነው ብለው ያምኑ ነበር።"[17] *Catholic Times* የተባለው መጽሔት ፖፑ ከኢጣልያ ፋሺስት አገዛዝ ጋር ስላደረጉት ወዳጃዊ አቋም ምክንያቱን እንዲኽ በማለት ይገልጣል፡-

> … ስለ ባለጌውና አሰልቺው ፋሺዝም ፖፑ ትዕግሥተኛ መኾናቸው እውነት አላቸው፤ እንዲሁም ሥልጣኑን አብዝቶ ለሚጠቀመው ለናዚ ፍልስፍና ትዕግሥተኛ መኾናቸውም እውነት አላቸው … በኢጣልያ ስድብ ወርዶባቸዋል፤ እንዲሁም የጀርመንንም አክራሪነትና ስደት ተሸክመዋል። ምክንያቱም የፋሺስትና የናዚ ሥርዐት፣ እንዲኹም ኢምፔሪያሊዝም ምንም እንኳ ከመጠን በላይ ሥልጣን መጠቀማቸው ክፉ ቢኾንም ከኮሚኒስት አስተዳደር የተሻሉ ናቸው … የእኛ ተልእኮ፣ አውሮፓን ከኮሚኒዝም የማዳን ተልእኮ ነው፤ በኮሚኒስት ሥርዐት ላይ የተቃውሞ ግንባርን ማቋቋም ነው። ማናቸውንም መሥዋዕትነት በመክፈል ከኢጣልያና ከጀርመን ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር አለብን።[18] ብሏል።

፫ኛ. የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሙሶሊኒንና የእርሱን የፋሺስት ደጋፊዎች ብታስቀይማቸው፣ በካህናት ላይ ተቃውሚቸውን እንደሚያነሡና የናዚን ዘዴ ይወስዳሉ ብለው ይፈሩ ስለ ነበር ነው።[19]

፬ኛ. ዋናው ምክንያት ፖፑ የሮማ ካቶሊክ እምነት በኢትዮጵያ በስፋት እንዲስፋፋ ተስፋ ማድረጋቸው ነበር። ዊሊያም ትሊንግ እንዳለው፡-

---

[15]Ibid፡ See *PRO*, FO 371, 20419, R1250/782/22, D. G. Osborne, British Consul, to Foreign of fice, Vatican City, February. 26, 1936.

[16]Binchy, *Op. Cit.,* p. 85.

[17]Baer, Op. Cit., p. 284. *Teeling, Op. Cit.*, p. 130. L. Salvatorelli, and G. Mira, Storia d'Italia nel periodo fascsta, Roma:Einaudi, 1959, 3rd ed. pp. 419-494.

[18]*The Catholic Times,* June 26, 1936.

[19]*The Manchester Guardian*, February 24, 1936. See also PRO, FO 371, 20419, R1250/782/22, D. G. Osborne to Foreign Office, Vatican City, February. 26, 1936. Baker, *Op. Cit.,* p. 290.

> የካቶሊክ እምነት በኢትዮጵያ ሊስፋፋ የሚችለው በኢጣልያ ድጋፍ ብቻ መኾኑን ፖፑ አምነውበት ነበር … እንደ እውነቱ ከኾነ ፖፑ ኃይላቸው ኹሉ በዐምባገነኖች መሪዎች ላይ ጥለው ነበር፡፡ እሳቸው የኢጣልያ ንጉሠ ነገሥታዊ አመራር ለእሳቸው ቤተ ክርስቲያን በተሸነፋት (የአፍሪቃ) ሀገሮች ኹሉ እንደምትስፋፋ በጥብቅ ያምኑ ነበር፡፡[20] ብሏል፡፡

በዚኹ ግምት ነው የሚላኖ ሊቀ ጳጳስ ካረዲናል ሹስተር ጦርነቱ ከተከፈተ ከጥቂት ቀናት በኋላ እ.ኤ.አ. ጥቅምት ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፰ ዐ.ም. የኢጣልያ ወታደሮችን በማወደስ እንዲኽ ያለው፡- "የኢጣልያ ወታደሮች የኢትዮጵያን በር ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና ለሮም ሥልጣኔ እየከፈቱ ነው፡፡"[21]

ኢትዮጵያ ከተሸነፈች ከስድስት ወራት በኋላ እ.ኤ.አ. ጥቅምት ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዐ.ም. ካርዲናል ቲሴራንት ለአንድ ጋዜጠኛ በሰጡት ቃለ ምልልስ በተሸነፈው የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ለካቶሊክ ሚስዮን ስለ ገጠመው ብሩኽ ዕድል እንዲኽ በማለት ተናግረዋል፡-

> ይኽን የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ማሸነፍ ለካቶሊክ ሚስዮኖች ትልቅ መስክ ከፍቶላቸዋል፡፡ ከዚኽ በፊት የእነሱ ሥራ በአቤሲኒያ በማይበገሩ የሞኒፊሳይት ካህናት ተስተጓጒሎ ነበር … የካቶሊክ ሚስዮናውያን ሥራ አኹን ኢጣልያ ከጀመረችው የማሠልጠን ሥራ ጋር እጅ በእጅ እየተጋገዙ ይሠራሉ፡፡[22]

ካርዲናል ቲሴራንት በቅርቡ በኢትዮጵያ ሊካኼዱ ስላቀዱት የሚስዮን ሥራዎች መርሐ ግብሮች በሰፊው አብራርተዋል፡፡ ምንም እንኳ ፖፑ በኢትዮ-ኢጣልያ ጸብ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ባይፈልጉና ገለልተኛ ለመምሰል ዝምታን ቢመርጡም፣ አንዳንድ ጊዜ ጦርነቱን በሚመለከት በሚናገሯቸው ጥቂት ንግግሮች የሚያሳዩት አቋም የሙሶሎኒ ወገንና መኾናቸውንና የፋሺስቱን አቋም የሚደግፉ መኾናቸውን በግልጽ ያመለክታሉ፡፡ ለጥቂት ጊዜያት ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ዝምታቸውን ትተው ስለ ኹለቱ ሀገሮች ጦርነት ተናግረዋል፡፡ ኹኖም ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የከፈተችው ጦርነት ትክክለኛ አለመኾኑን ፈጽሞ አልተናገሩም፡፡

---

[20]Teeling, *Op. Cit.*, pp. 128-129. Cf. G. A. Garratt, *Mussolini's Roman Empire*, London: Penguin Books Ltd., 1938, pp. 106-107.

[21]Popolo d'Italia, October 29, 1935. See also Toynbee, *Op. Cit.*, 104. Binchy, *Op. Cit.*, p. 679.

[22]Gazetta del Popolo, October. 22, 1936. An English translation of the article on the interview is de posited in IMC, Archives at Edinburgh House. IMC, Box 262, file,- "Foreign Office 1935-1943", folder – "1936/38".

እ.ኤ.አ. ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፴፰ ዐ.ም. ከመላዋ ኢጣልያ በሮም የተሰበሰቡትን ፸፻ የሚያኽሉ የአንደኛው ዐለም ጦርነት ተዋጊዎችን ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ተቀብለው አነጋግረዋል፡፡ እንዲኹም ራሳቸው ፖፑ ቅዳሴ ቀድሰውላቸዋል፡፡ ከእነዚኹ ውስጥ አብዛኞቹ ወደ ኢትዮጵያ ለመዋጋት የሚኼዱ ነበሩ፡፡ ፖፑ ይኽን ያደረጉት ወደ ኢትዮጵያ ለሚኼዱት ለወታደሮቹና ለፋሺስቱ መንግሥት የሞራል ድጋፍ ለመስጠት መኾኑ ግልጽ ነበር፡፡[23]

እ.ኤ.አ. ሐምሌ ፳፰ ቀን ፲፱፻፴፰ ዐ.ም. ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ስለሚደረገው ጦርነት ጥቂት በመጥቀስ ይፋዊ ንግግር አድርገው ነበር፡፡ በንግግራቸው ላይ ፖፑ ከ፲፰፻፴፰ ዐ.ም. እስከ ፲፰፻፷ ዓ. ም. ድረስ የካቶሊክን እምነት በኢትዮጵያ የሰበከና የፖፕ እንደራሴ የነበረ የጁስቲኖ ዲ ጃኮቢስን የሞራል ዋጋና ቅድስና በይፋ ዐወጁ፡፡[24] ከዚያ በፊት ስለ ዲ ጃኮቢስ ምንም የተለየ ነገር ተሰምቶ አያውቅም፡፡ ከዚያ በፊት ስለዚህ ሰው ለቅድስና የሚያበቃ ነገር አልተሰማም፡፡ በሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዐት መሠረት በሕይወታቸው የተለየ ደግነትና ቅድስና ያሳዩ፣ ከሞቱም በኋላ ተአምራትን ያሳዩ ሰዎች ብቻ ናቸው ለብፅዕና ማዕርግ የሚታጩትና የሚሰጣቸው፡፡ ይኽም ከብዙ ምርምርና ፈተና በኋላ ነው ብፅዕና የሚሰጣቸው፡፡[25] ዲ.ጃኮቢስ ግን በሐዋርያዊ አገልግሎታቸው ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው በ፷ ዐመት ዕድሜአቸው ታመው በተፈጥሯዊ ሞት ነው የሞቱት፡፡ ጂ ሳልቬሚኒ እንዲኽ ሲሉ ተችተዋል፦ "ወንድም ጁስቲን ዲ ጃኮቢስን ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ለብፅዕና ማዕርግ ከፍ ከማድረጋቸው በፊት ፸፭ ዐመታት አልፈዋል፡፡ ታዲያ በዚህ ጊዜ ውስጥ ዲ ጃኮቢስ ምንም ተአምር አላሳዩም፡፡"[26] የዚኽ ክብረ በዐል ቁምነገር ምን ነበር? ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ለኚኽ መነኵሴ ብፅዕና ለመስጠት ለምን ይኽን ጊዜ መረጡ? አንዳንድ ሰዎች እንደሚያስቡት "ፖፑ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የምታካኺደውን ጦርነትና ኢትዮጵያን ይዘው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን መስፋፋትን ለማጋነን ያደረጉት ዘዴ ነው" ይላሉ፡፡ ፖፑ በዚያ ክብረ በዐል ላይ ለነበሩት ካህናት ሲናገሩ "እነሱ ወደ አፍሪካ በደረሱ ጊዜ የዲ. ጃኮቢስን ጀግንነት እንዲከተሉ አጥብቀው አደፋፍረዋቸዋል፡፡"[27] በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሳልቬሚኒ እንደሚሉት "የዚኽ በዐል አከባበር የሙሶሊኒ ጦርነት ፕሮፓጋንዳ ነው ተብሎ ይተረጐማል፡፡"[28] በክብረ በዐሉ ላይም ፖፑ ሲናገሩ እንዲህ አሉ፦

---

[23]Gaetano Salvemini, "*The Vatican and the Ethiopian War*", in F. Keen, ed., Neither Liberty Nor Bread, New York: Harper, 1940, p. 195.

[24]Rome, *Op. Cit.*, p. 74. Baer, *Op. Cit.,* p. 125. Kifelew Zelake, "The History of the Independence of the Ethiopian Church," Ph.D. Thesis, University of Athens, 1969, pp. 53-54 (in Greek).

[25]John L. Mackenzie, *The Roman Catholic Church,* London: Weidenfeld, and Nicolson, 1969, pp. 227- 28.

[26]Salvemini, *Op. Cit.*, 1953. **ስለ ዲ ጃኮቢስ ሚስዮናዊ ሥራ ተመልከቱ** D. Crummey, *Priests and Politicians: Protestant and Catholic Missions, in Orthodox Ethiopia 1830 – 1968*. Oxford, Ox ford University Press,1972, pp. 59-114.

[27]Rome, *Op. Cit.*, p. 75.

[28]Salvemini, *Op. Cit.*, p. 195.

በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል ጥቁር ደመና አንዣቧል፡፡ ምን እንደሚኾን አይታወቅም፤ ቁምነገር ወይም ምሥጢራዊ ነገር ሊኾን ይችላል፡፡ ወደፊትም ብዙ ደመና ይመጣ ይኾናል … እናምናለን፤ በክርስቶስ አገዛዝ ውስጥ በክርስቶስ ሰላም ኹልጊዜ እናምናለን፡፡ ማናቸውም ያለ እውነትና ያለ ትክክለኛ ፍርድ በእርሱ ቸርነት ምንም ነገር እንደማይኾን ሙሉ እምነት አለን፡፡[29]

ፖፑ የሚመለከታቸው ሀገሮች ከጦርነት እንዲወገዱና ለልዩነታቸው በሰላማዊ መንገድ እንዲፈልጉ አንዲት ቃል እንኳ አልተናገሩም፡፡ ኢትዮጵያ በኢጣልያ እንድትያዝ ይፈልጋሉ!

እ.ኤ.አ. ነሐሴ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፭ ዐ.ም. ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ በስብሰባ ላይ የነበሩትን የዐለም ዐቀፍ ኮንግሬስ ነርሶችን ተቀብለው አነጋግረው ነበር፡፡ ለእነሱም ንግግር ሲያደርጉ በተለይ የኢትዮ-ኢጣልያ ጦርነትን በመጥቀስ እንዲኽ አሉ፡-

በውጭ ሀገር ስለ ድል አድራጊነት ጦርነት፣ ስለ ወረራ ጦርነት ሲወራ እንሰማለን … ለማሸነፍ የሚደረግ ጦርነት የማይገባ ጦርነት ነው … በሌላ በኩል እዚኽ በኢጣልያ ይኽ የተባለው ጦርነት ራስን የመከላከልና ከተደጋጋሚ ጥቃት ድንበርን ለመጠበቅ የሚደረግ ጦርነት ስለኾነ ትክክለኛና ተገቢ ጦርነት ነው ይባላል፡፡ በኢጣልያ በየጊዜው እየጨመረ የሚኼደው የሕዝብ ቍጥር እየበዛ ስለኼደ ጦርነት አስፈላጊ ነው ተብሏል፡፡ ራስን ለመከላከልና ሀገር የሚያስፈልጋትን ቁሳቁስ ለማሟላት የሚደረግ ጦርነት ራሱን ትክክለኛ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ይኽ እውነት ከኾነ እውነትን ከመግለጽ በስተቀር ምንም ማለት አይቻልም፡፡ ይኽ የመስፋፋት ፍላጎት ካለ፣ ድንበርን የመጠበቅ ፍላጎት ካለ … ይኽን ችግር ለመፍታት ከጦርነት ይልቅ ሌላ መፍትሔ እንደሚፈለግ ተስፋ እናደርጋለን … የመስፋፋቱ ፍላጎትና የድንበር ጥበቃውም ሐቅ ከኾነ ራስን መከላከል መጠን ሊኖረው ያስፈልገዋል፡፡ ከነቀፋ ለመዳንም መጠነኛነትን መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡[30]

---

[29] ፖፑ በንግግራቸው ምክንያት በውጭ ሀገር በደረሰባቸው ጠንካራ ትችት ብዙ የተቸገሩ ይመስላል፡፡ ስለዚኽ ቫቲካን አንዳች ምክንያት ለመፈለግ ሞከሩ፡፡ Osservatore Romano የተባለው የካቶሊክ ጋዜጣ አንዳንድ ጋዜጦች የፖፑን ንግግር በሙሉ ሳይኾን አሳጥረው በመጻፍ "ተሳስተዋል" በማለት ኮንኗል፡፡ አከራካሪ ስለኾነው ነጥብ ሲገልጽ "የመስፋፋት ፍላጎት በራሱ መብት አይደለም፤ ይኽ የሚያሳስብ እውነት ነው እንጂ፡፡ ይኽ ግን ሕጋዊ መብት አይደለም፡፡" በማለት የፖፑን ንግግር ለማስተካከል ሞክሯል፡፡ Osservatore Romano, Augest. 30, 1935. See also *The Times,* London, August. 31, 1935, P.10.

[30] Baer, *Op. Cit.*, p. 286. See also *The Times*, London, August. 29, 1935, *The Manchester Guardian*, August. 29, 1935. Toynbee, Op. Cit., p. 102.

ይኽ ንግግር በኢጣልያና በውጭ ሀገር በስፋት ተነገረ፤ ይኽ ንግግር ኢጣልያ ለመስፋፋት ለምታደርገው ፍላጎት ትልቅ ድጋፍና ርጎራጌ እንደኾነ በኹሉ ዘንድ ታወቀ፡፡ በዚኽ ምክንያት የውጭ ሀገር መገናኛ ብዙኃን ፖፑን በጥብቅ ነቅፈዋቸዋል፤ የፋሺስት መገናኛ ብዙኃን ግን ፖፑን በከፍተኛ ኹኔታ አወድሰዋቸዋል፡፡[31] ፖፑ በአገላለጻቸው ላይ "በኢጣልያ የሕዝብ ብዛት እየጨመረ ስለኼደ ጦርነቱ ትክክለኛ ነው የሚሉ አሉ፡፡" በማለታቸው የሙሶሊኒን ሐሳብና በኢትዮጵያ ላይ ለከፈተው ጦርነት ያቀረበውን ክርክር በግልጥ አንጸባርቀዋል፡፡ በእሳቸው እምነት ጦርነቱ ትክክል ነው፡፡ ኾኖም እሳቸው የለመኑት ጦርነቱ መጠነኛና ልክ እንዲኖረው ብቻ ነበር፡፡ ፖፑ "የመስፋፋት ፍላጎት እውነትና ሊታሰብበት የሚገባ መኾኑን" አምነዋል፡፡ በዚኽም የፋሺስትን የመስፋፋት መመሪያ አጽድቀውታል፡፡ ሳልቬሚኒ የፖፑን ንግግር በመተቸት እንዲህ ይላል፡-

> አንድ ሰው በጥልቅ ሳይመረምር ይኽን ለነርሶቹ የተናገሩትን የፖፑን ንግግር ለሚያነብ ጦርነት ወንጀል ነው ያሉ ይመስላል፡፡ እንደ እውነቱ ከኾነ ግን ይኽንን ጦርነት አላወገዙም፡፡ እንዲያውም ይኽ ጦርነት ራስን የመከላከል ጦርነት ነው በማለት አጽድቀውታል፡፡ በተጨማሪ ግን ሙሶሊኒ ራስን ለመከላከል በሚያደርገው ጦርነት መጠንና ልክን እንዳያልፍ ብቻ ተማጽነዋል፡፡[32]

በዚኽ ንግግር ላይ ፖፑ ስምምነትን ስለ መጠበቅ ግዴታና ኢትዮጵያና ኢጣልያ በተስማሙበት መሠረት ልዩነታቸውን በሽምግልና ስለ መፍታት ሓላፊነት ጥቂት እንኳ አልጠቀሱም፡፡[33]

እንደገና ፖፑ እ.ኤ.አ. መስከረም ፯ ቀን ፲፱፻፴፭ ዓ.ም. የመንግሥታቱ ማኅበር ጠቅላላ ጉባዔ ተሰብስቦ ስለ ኢትዮ-ኢጣልያ ግጭት በጄኔቫ በሚነጋገርበት ዕለት ፖፑ ሌላ ንግግር አደረጉ፡፡ ፲፭፻ የሚያኽሉ የቀድሞ ወታደሮች የፍራንኮ-ኢጣልያንን ስምምነትና የላቫልንና የሙሶሊኒን መመሪያ ለመደገፍ በሮም ተሰብስበው ነበር፡፡ እነዚኽ ወታደሮች ከፖፑ ቡራኬ ለመቀበል በኼዱ ጊዜ ፖፑ በአደረጉት ንግግር እርሳቸው ስለ ሰላም እንደሚጸልዩ አረጋገጡላቸው፡፡ ፖፑ ለቀድሞ ወታደሮች ሲናገሩ እንደ አንድ የዐለም ዐቀፍ ቤተ ክርስቲያን አባት ወይም እንደ አንድ የዐለም ዐቀፍ ድርጅት (የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን) አባት ሳይኾን እንደ አንድ ኢጣልያዊ ያውም እንደ አንድ ሀገር ወዳድ ኢጣልያዊ ነበር የተናገሩት፡፡ ከተናገሩት ጥቂቱ የሚከተለው ነው፡- "ከሰላም ጋር የጥሩው፣ የታላቁና የመልካሙ የኢጣልያ ሕዝብ፣ የእኛ ሕዝብ ተስፋ፣ ፍላጎትና የሚያስፈልገው ነገር ኹሉ እንዲሟላና የጸደቀ እንዲኾን እንመኛለን፡፡ የሀገራችንም መብት እንዲጸድቅና እንዲረጋገጥ እንመኛለን፤ ኾኖም ኹሉም በሰላምና በትክለኛ ፍርድ

[31]Binchy, *Op. Cit.*, p. 640.

[32]Salvemini, *Op. Cit.*, p. 197

[33]ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ፳፱፡፡

እንዲኾን እንመኛለን፡፡”[34]

> እዚኽ ላይ ፖፑ ለኢጣሊያና ለፋሽስት መንግሥት ያላቸውን ፍቅርና ልባዊ ድጋፍ በግልጥ ገልጸዋል፡፡ ፖፑ እዚኽ በንግግራቸው ውስጥ ምንም የዲፕሎማሲ ቋንቋ አልተጠቀሙም፡፡ እሳቸው በግልጽ ነው የተናገሩት፡፡ “የታላቁና የመልካሙ ሕዝባችን ተስፋ፣ ፍላጎት (የመስፋፋት ፍላጎት) እና የሚያስፈልገው ነገር ኹሉ እንዲሟላና የጸደቀ እንዲሆን” ለኢጣልያ ተመኝተዋል፡፡ ሳልቬሚኒ እንደ ተቸው “በመጨረሻ ላይ ‹ሰላምና ትክክለኛ ፍርድ› የሚሉት ቃላት የገቡት ኪኒኑን ለማጣፈጥ ነው፡፡”[35] ብሏል፡፡

የኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያን ከመውረሩ በፊት በዋዜማው እ.ኤ.አ. ጥቅምት ፪ ቀን ፲፱፻፳፰ ዐ.ም. የኢጣልያ ፋሺስት መንግሥት ታላቅ የሕዝብ ሰልፍ በመላዋ ኢጣልያ በአደረገ ጊዜ በመላዋ ኢጣልያ የሚገኙ የኹሉም የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ደወሎች ለረጅም ጊዜ ተደወሉ፡፡ ይኽም የኾነው ሕዝቡን ለመቀስቀስና በዐሉንም ለማክበር ነበር፡፡ በወቅቱ የሎንዶን ታይምስ (Times) ጋዜጣ ዜና አቀባይ እንደ ዘገበው፣ በዚኹ ታላቅ ሰልፍ ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን መውረሩን በይፋ በማወጁ በሮም ከተማ “አንድ ሺ የሚያኽሉ የቤተ ክርስቲያን ደወሎች›› አየሩን አናወጡት፡፡” ብሏል፡፡ በዚያን ቀን የቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራል ካምፓኖኔ የተባላው ትልቁ ደወልና አምስቱ አነስተኛ ደወሎች ሙሶሎኒ የኢትዮጵያን መወረር በማወጅ ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ኹሉ ይጮሁ ነበር፡፡[36]

ዳንኤል ቢንቺ Osservatore Romano[37] የተባለው የቫቲካን ጋዜጣ ደወሎቹ የተደወሉት ለማታ ጸሎት ነው በማለት ያደረገውን ክርክር በመቃወም “የተሰጠው ዜና ፈጽሞ ስሕተት ነው፤” ሲል አጥላልቶታል፡፡ የማታ ጸሎት ደወል የሚደወለው በ፲ ሰዐት ተኩል ላይ ነው፡፡[38] በሌላ በኩል ደግሞ ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛን የሙሶሊኒ ደጋፊ ናቸው ብሎ በጥብቅ ይከሳቸው የነበረው ሳልቬሚኒ “በቅዱስ ጴጥሮስ ለማታ ጸሎት ደወሉ የሚደወለው ፲ ሰዐት ከ፲፫ ደቂቃ ነው እንጂ ከዚያ በፊት አይደወልም” በማለት ይከራካራል፡፡ “የኦሰርቫቶሬ ሮማኖ ጸሐፊ የፖፑን ኃላፊነት ለመደበቅ ሞከሯል፣ እነሱ ራሳቸው እውነት መኾኑን የሚያውቁትን ሐቅ ይደብቃሉ፡፡ ይኽ በእግዚአብሔር ክብር

---

[34]See extract of the speech in Baer, *Op. Cit*., p. 287. Salvemini, *Op. Cit*., p. 198. Toynbee, *Op. Cit*., P. 102. Civilta Cattolica, 3, 1935, p. 638.

[35]Salvemini, *Op. Cit.*,198. New Times and Ethiopia News እንደ ጻፈው “ፖፑ የመከላከል ጦርነትንና የማጥቃት ጦርነትን አነጻጽረው ሲጽፉ ኹለቱም ጦርነቶች ተገቢዎች ናቸው፡፡” *New Times and Ethiopia News*, July 4, 1936. ይኽ ትክክል መኾኑ አይታወቅም፡፡

[36]*The Times* (London), October. 3, 1935. See also *New Times and Ethiopia News,* October. 17, 1936.

[37]Osservatore Romano, October. 7-8, 1935. Civilta Cattolica, October. 4, 1935, P. 164.

[38]Binchy, *Op. cit.*, p 641.

ላይ መዋሸታቸው ነው።"[39] ሲልም ጽፏል።

ሳልቬሚኒ እንደሚለው በቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራል አካባቢ ለብዙ ዐመታት የምትኖርና የደወሎቹንም አደዋወል የምታውቅ አንዲት የሮም ከተማ ሴት እንዳረጋገጠችለት የማታ ጸሎት የሚደወለው ከትናንሾቹ ደወሎች በአንዱ ብቻ ነው፤ ያውም ለጥቂት ጊዜ ነው። ነገር ግን እ.ኤ.አ. ጥቅምት ፪ ቀን ፲፱፻፴፭ ዐ.ም. ኹሉም ደወሎች ነበር የተደወሉት፤ ያውም በከፍታ ድምፅና ለረጅም ጊዜ ከሌሎቹ የሮም ደወሎች ጋር የሙሶሊኒ ንግግር እስከሚያበቃ ድረስ ነበር።[40]

ሳልቬሚኒ እንደሚለው "በቤተ ክርስቲያን ሕግ የቤተ ክርስቲያን ደወሎች ላልተቀደሱ ነገሮች ጥቅም ላይ አይውሉም በተለይ በጳጳሱ ፈቃድ ካልኾነ በስተቀር።"[41] ቀጥሎም እንዲህ ይላል፡- "የሮም ሀገረ ስብከት የፖፑ ሀገረ ስብከት ነው፤" ስለዚኽም "ፖፑ ካልፈቀዱ የሮም አብያተ ክርስቲያን ደወሎች ኢትዮጵያን ለመውረር ለተደረገው የፋሺስት ሰላማዊ ሰልፍ ጊዜ ሊደወሉ አይችሉም ነበር።"[42]

የተባበሩት መንግሥታትን ቃል ኪዳን በመጣስ ኢጣልያ ኢትዮጵያን በመወረሯ የመንግሥታቱ ማኅበር በኢጣልያ ላይ ማዕቀብ በጣለ ጊዜ፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት፣ ካህናትና የካቶሊክ ሚድያዎች የመንግሥታቱን ማኅበር ውሳኔ አጥብቀው አውግዘዋል።[43] በእነርሱ አነጋገር ማዕቀብ ግብረ ገብነት የጐደለው ተግባር ነው።[44] በማዕቀቡ እጅግ የተቸገረችውና ቅር የተሰኘችው ቫቲካን ማዕቀቡ እንዲነሣ በስተጀርባ ኾና ትሠራ እንደነበረ በብዙ ቦታ ተነግሯል። ስለዚኽ የፖፑ እንደራሴዎች በደቡብ አሜሪካ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች በኾኑት መንግሥታት ዘንድ ማዕቀቡ እንዲነሣ ለማድረግና "በጄኔቫ ስለዚኹ ጉዳይ እንዲፈርሙ ያግባቡ እንደ ነበርና ብዙ ሙከራ እንዳደረጉ ተነግሯል።"[45] የኋላ ኋላ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ስለ ፈጸመችው ወረራ በመንግሥታቱ ማኅበር ዘንድ ውይይት ላይ በቀረበና አባላቱም ለማኅበሩ ቃል ኪዳን ድጋፍና ታማኝነትን በገለጹ ጊዜ የላቲን አሜሪካ ሀገሮች ተወካዮች "ለመንግሥታቱ ማኅበርና ለኢትዮጵያ ድጋፋቸውን ለመስጠት ወደ ኋላ ይሉ ጀመር።" ለኢጣልያም የነበራቸው ስሜት ወዳጃዊ ነበር።[46]

---

[39] Salvemini, *Op. cit.*, pp. 198-199.

[40] Ibid, p. 199.

[41] Ibid, p. 193.

[42] Ibid, p. 199.

[43] A. C. Jemolo, *Church and State in Italy 1850-1950*, trans. by D. Moore, Oxford: Basil Blackwell, 1960, p. 260. Sturzo, *Op. cit.*, p. 503.

[44] Sturzo, *Op. cit.*, p. 503.

[45] Teeling, *Op. cit.*, p. 253. See also Binchy, *Op. cit.*, pp. 642-643.

[46] Walters, *A History of the League of Nations*, II, p. 650.

የቫቲካን ልሣን የኾነው Osservatore Romano የተባለው ጋዜጣ በኢትዮ-ኢጣልያ ጦርነት ላይ ገለልተኛ መስሎ ለመታየት ቢሞክርም፣ "በማዕቀቡ ላይና ኢጣልያን በሚጐዳ ጉዳይ ላይ ኹሉ አጠቃላይ ጥላቻንና ተቃውሞውን አሳይቷል።"[47] ይኽ ጋዜጣ ኢጣልያ ወራሪ ነች በማለት ተቀብሎም አያውቅ።[48]

በሌላ በኩል ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ለአደረገችው ዘመቻ ቫቲካን ለኢጣልያ መንግሥት መጠኑ የበዛ የገንዘብ ርዳታ ሰጥታለች ተብላ ተከሳለች።[49] አንድ A. E. Guillaume የተባለ ሰው Revue Politique Parlementaire ላይ በጻፈው መጣጥፍ ከነሐሴ ፲፱፻፳፰ ዐ.ም. እስከ ሰኔ ፲፱፻፳፱ ዐ.ም. ድረስ ባሉት ዐሥር ወሮች ውስጥ ቫቲካን ፹፱ ሚልዮን ፍራንክ ለኢጣልያ መንግሥት እንደ ሰጠች ጽፏል። እርሱ እንዳረጋገጠው ይኽ ገንዘብ የተገኘው ከኢጣልያ ውጭ የቅዱስ ጴጥሮስ ዲናር ከሚባለው ነው። ይኽ ገንዘብ ከውጭ ሀገር ወደ ኢጣልያ የመጣው በውጭ ምንዛሪ በቫቲካን የዲፕሎማቲክ ሻንጣ ነበር ብሏል።[50] ኾኖም የዚኽን ትችት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልቻልኩም። እንዲኹም ቫቲካን ውጭ ሀገር ያከማቸችውን የውጭ ገንዘብ ከውጭ ሀገር በውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ለኢጣልያ ሊራ ትልቅ ድጋፍ እንዳደረገች ይታመናል።[51] በግልጽ እንደሚታወቀው በዚያን ጊዜ ዋናው የቫቲካን የገቢ ምንጭ የሚገኘው የቅዱስ ጴጥሮስ ዲናር ከሚባለው ነበር። አብዛኛውም ይመጣ የነበረው ከኢጣልያ ውጭ ነበር።

በኒው ዮርክ የIMC ዋና ጸሐፊ የነበረው ዋርንሹስ የገለጸውን መመልከት በጣም ጠቃሚ ነው። ዋርንሹስ እንዳለው፦

> የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ኢጣልያ በአፍሪካ በምታደርገው የጦርነት ጀብድ በፍጹም መግባባት እየሠሩ ናቸው። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሚሸነፉት ሀገሮች ማለት በመላ ኢትዮጵያ ኹሉንም ሊይዙ ከቻሉ ሙሉ የሚስዮን ሥራዋን እንደምታካኺድ ሙሉ እምነት አላት።[52]
> ቫቲካን ለኢጣልያ መንግሥት ስለምታደርገው ድጋፍ ዋርንሹስ እንዲኽ ይላል፦
> እንደ ሚመስለው (የካቶሊክ) ቤተ ክርስቲያን ለተለያዩ በኢጣልያ ያሉ ሀብት

[47]*PRO*, FO 371, 20419, fol., 300, D. G. Osborne, British Consul to the Vatican, to Eden, Rome, March 12, 1936.

[48]Ibid,FO371,20179, J2944/180/1, D. G. Osborne to Foreign Office, Rome, April 3, 1936.

[49]*New Times and Ethiopia News*, April 30, 1938.

[50]*Revue Politique et Parlementaire,* Paris, October. 10, 1936. See also PRO, FO 371, 419, R6476/782/22, Mal let to A. Eden, Rome, October. 27, 1936. PRO, FO 371, 20410, R2422/226/22, Admiralty to Foreign Office, April 29. 1936.

[51]A. McLeish and K. G. Grubb, "*Situation of Missions in Ethiopia*," IMC, Edinburgh House, file – "Religious Freedom: British Group".

[52]*IMC*, Box 262,, folder - "Dr. A. J. Warnshuis (USA)", A. J. Warnshuis to J. H. Oldham, New York, Nov. 29, 1935.

ያላቸው የቤተ ክርስቲያን ድርጅቶች ኹሉ ለኢጣልያ መከላከያ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ትእዛዝ ሰጥታለች፡፡ ይኽ አስተዋጽኦ ምን ያህል ብዙ እንደ ኾነ አይታወቅም፡፡ ኾኖም ይኽ ኢጣልያ በአፍሪካ የምታደርገውን ጦርነት ለማካኼድ የሚያስችላት ትልቅ ምንጭ እንደሚኾን ብዙዎች ያምናሉ፡፡[53]

ኢጣልያ የፈረመችውን የዐለም ዐቀፉ ቃል ኪዳንን በመጣስ ወታደሮቿ (የጦር አውሮፕላኖቿ) የቀይ መስቀል አምቡላንሶችን ኾን ብለው በቦምብ መደብደባቸውንና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የመርዝ ጋዝ በብዛት በመርጨታቸው ብዙ ሕዝብ፣ ሕፃናትና ሴቶች ከማለቃቸውም በላይ እንስሳትና የዱር አራዊትም ጭምር በብዛት አልቀዋል፡፡ ይኽንን ኢሰብአዊ ተግባር ዐለም ኹሉ ሲያወግዘው ፖፑ በሚታወቀው ምክንያት (ኢጣልያንን በመደገፍ) አንዲትም ቃል አልተነፈሱም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፖፑ የኢጣልያ ወታደሮች ኢትዮጵያን በማሸነፋቸው ደስታቸውን በመግለጻቸው ብዙ ሰዎች ፖፑን አጕልተው መኰነናቸውና መንቀፋቸው የሚያስደንቅ አይደለም፡፡ ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ድሉን ሲገልጹ "እጅግ የሚያስደስት ድል" ብለውታል፡፡ እ.ኤ.አ. ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፴፮ ዐ.ም. ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከኢትዮጵያ ተሰደው ከኼዱ ከዐሥር ቀን በኋላና የኢጣልያ ወታደሮች ዐዲስ አበባን ከያዙ በኋላ ፖፑ ለካቶሊክ ዐለም ዐቀፍ መገናኛ ዐወውደ ርእይ ባሰሙት ንግግር እንዲኽ አሉ፡- "ይኽ ቀን ትልቁና መልካሙ ሕዝብ ለምንመኘው ሰላም ያገኘው እጅግ ከሚያስደስት ድል ጋር ተጋጥሟል፡፡"ሲሉ ተናግረዋል፡፡[54]

በኢጣልያ ጦር ወረራና በማሸነፏ የእኚህ ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ መደሰት በእያንዳንዱ ሀገር የመደናገጥንና የመደነቅን ስሜት እንዲሁም ንዴትን ፈጥሯል፡፡ ይኽም ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ በአገኘችው ድልና በአፍሪካ የኢጣልያ ትልቅ መንግሥት በመቋቋሙ እንደ አንድ ትልቅ የደስታ መግለጫ ኾኖ ተቆጥሯል፡፡[55] በኢጣልያ "የፋሺስት መገናኛ ብዙኃን የፖፑን ንግግር በላቀ ደስታ ነበር የተቀበሉት፡፡ ይኽም የፖፑ ንግግር የድሉ ማሳረጊያና የኢጣልያ ጦርን ማመስገኛ ኾኖ ነው የተቆጠረው፡፡"[56] ኾኖም በሌሎች ሀገሮች በተለይም በእንግሊዝ ሀገር የፖፑ ንግግር ታላቅ ውግዘት ገጥሞታል፡፡ የሳውዝዋርክ ጳጳስ ለሀገረ ስብከቱ ስብሰባ ባደረጉት ንግግር እንዲኽ ብለዋል፡-

---

[53] <u>*IMC*</u>. <u>*Op. cit*</u>.

[54] This extract is taken from the *New Times and Ethiopia News,* "The Silence of His Holiness," June 13, 1936. The full text of the speech is found in *Civilta Catolica,* 2, 1936, p. 422.

[55] The extract of the speech is taken from the *New Times and Ethiopia News,* June 13, 1936. The full text of the speech is found in *Civilta Cattolica*, 2, 1936, p. 422.

[56] Binchy, *Op. cit.*, p. 649.

እኔ የምናገረው በአዘነ ልብ ነው፤ በትልቅ ወንጀልና ቃል ኪዳንን በመጣስ የተገኘ ድል፣ ኾን ተብሎ የቀይ መስቀል አምቡላንሶችን በቦምብ በመደብደብና በሕዝብ ላይ የመርዝ ጋዝን በመርጨትና ምንም መከላከል የማይችሉትን ሕዝቦች በማሠቃየት የተገኘን ድል እንደ ትልቁና የመልካሙ ሕዝብ አስደሳች ድል ተብሎ ተወድሷል፡፡ በክርስቶስ ስም ከእንደዚኽ ያለ ንግግር ራሳችንን እናርቃለን፤ የቃል ኪዳኑን ጥሰት በቀላሉ እንዳናይና ጉልበተኛው ደካማውን ሲያጠቃ ዝም እንዳንል መጠንቀቅ አለብን፡፡[57] ብለዋል፡፡

በሌሎች ሀገሮች የካቶሊክ መገናኛ ብዙኃን ጭምር በፖፑ ንግግር እጅግ በጣም አፍረዋል፡፡[58] ኾኖም አንዳንድ ጸሐፊዎች ለማረጋገጥ እንደ ሞከሩት የፋሺስት ባለሥልጣኖች ፖፑ በሙሉ ልባቸው ኢጣልያንን እንዲደግፉና የመንግሥቱን መመሪያ በመደገፍ በይፋ እንዲያውጁ በፖፑ ላይ ብዙ ተፅዕኖ ያደርጉባቸው እንደነበረ ጽፈዋል፡፡[59] ኾኖም ዳንኤል ቢንቺ እንዳረጋገጠው ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ከማናቸውም አቅጣጫ በሚመጣ የመናገር ውሳኔ የራሳቸው ብቻ ውሳኔ ነው፡፡ በማያጠራጥር ኹኔታ በውስጣቸው የነበረው የኢጣልያዊነታቸው ስሜታቸው ነበር ገፋፍቶ እንዲናገሩ ያደረጋቸው፡፡ ሀገር ወዳዱ የሎምባርዲ ልጅ አቺሌስ ራቲ ነው ሀገሩ በመደሰቷ ተደስቶ የተናገረው … የፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ለኢጣልያ የነበራቸው ፍቅር እጅግ ጥልቅ ነበር፡፡ በዚኽ ጊዜ ይኽ ግብታዊ ስሜት ነበር ያንን አስተዋይነት የጐደለውን ንግግር እንዲያደርጉ ያደረጋቸው፡፡[60]

ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ስለ ኢጣልያ እንደዚኽ ያለ ስሜት ስለ ነበራቸው ነበር፣ ፋሺስት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በተለይ እ.ኤ.አ. የካቲት ፲፱-፳፩ ፲፱፻፴፯ ዐ.ም. በሦስት ቀናት ውስጥ የፈጸመውን ጭፍጨፋ ላለመስማት ኾን ብለው ጆሮአቸውን ያደነቆሩት፡፡ ይህንን ፫፻ በሚኾኑ ንጹሐን ኢትዮጵያውያን ላይ የተፈጸመውን የጭካኔ ጭፍጨፋ ካቶሊክ ያልኾኑት ሰዎች ብቻ ሳይኾኑ በመላው ዐለም የነበሩ ካቶሊኮች ጭምር ፖፑ በማውገዝ አንዳች ንግግር ያደርጋሉ ብለው ጠብቀው ነበር፡፡ ፖፑ ግን ስለዚኽ ምንም ቃል አልተነፈሱም፡፡[61]

ስለዚኽ ፋሺስት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመችው ወረራ እንደተሳካላት የኢጣልያን ድልና በኢትዮጵያ ላይ ያለውን ግዛት በማወቅ ያወጀችው የመጀመሪያዋ አገር ቫቲካን ነበረች፡፡ "ይኽንም አርአያ በመከተል ብዙ ሀገሮች … ኢትዮጵያ የኢጣልያ ግዛት

[57]Roome, *Op. cit.*, p. 75.
[58]Binchy, *Op. cit.*, p. 649.
[59]Teeling, *Op. cit.*, p. 129.
[60]Binchy, *Op. cit.*, p. 650.
[61]Teeling, *Op. cit.*, pp. 3-4

መኾኗን አወቁ።"[62] ከዚህም ሌላ የኢጣልያ ንግሥት የኢትዮጵያ ንግሥተ ነገሥታት ተብላ በታወጀች ጊዜ ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ የወርቅ አበባ አበርክተውላታል።[63] ኾኖም ምንም እንኳ ሙሶሊኒ ፖፑ ቪክቶር ኢማኑኤልን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አድርገው ዘውድ እንዲጭኑለት አጥብቆ ቢጠይቃቸውም ፖፑ ይኽን ለማድረግ አልፈለጉም ምናልባትም በፖሊቲካ ምክንያት ይኾናል።[64]

## ፫. ስለ ኢጣልያ ወረራ የኢጣልያ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች አቋም

የኢጣልያ ካህናት ጳጳሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ካርዲናሎች ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የከፈተችውን ጦርነት በመደገፍ ግልጽ የኾነ አቋም ወስደዋል። እነዚኽ የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ለፋሺስት ኢጣልያ መሪዎችና ለወታደሩ ኢትዮጵያን ለመውረር ለሚያደርጉት ጥረት ኹሉ ማናቸውንም የሞራልና የቁሳቁስ ድጋፍ አድርገዋል።[65] በማናቸውም አጋጣሚ ጊዜ እነዚኽ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካርዲናሎች፣ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት የሙሶሊኒን የጦር መመሪያ በመደገፍ ትምክህተኝነት የተሞላ ንግግር ያደርጉ ነበር። ሳልቬሚኒ በየጊዜው በኢትዮጵያ ላይ የሚደረገውን ጦርነት በመደገፍ የዐርበኝነት ንግግር ያደርጉ የነበሩትን ፳፫ የሚኾኑ የኢጣልያ ሊቃነ ጳጳሳትንና ጳጳሳትን ስም ዝርዝር ይሰጣል።[66] በኢጣልያ እ.ኤ.አ. ከሚያዝያ ፲፱፻፳፰ ዐ.ም. ጀምሮ በተደረጉ በአንዳንድ የሃይማኖት ስብሰባዎች ኹሉ መላው ካህናት በመግቢያውና በመዝጊያው ላይ ለሙሶሊኒ ታማኝነትንና ለመመሪያው ድጋፍን በታላቅ ስሜት ይሰጡ ነበር። እ.ኤ.አ. መስከረም ፫ ቀን ፲፱፻፳፰ ዐ.ም. ብሔራዊ ዩካሪስቲክ ኮንግሬስ (ስብሰባ) ተደርጎ ነበር፤ በዚኽ ስብሰባ ላይ የፖፑ እንደራሴ፣ ፲፱ ሊቃነ ጳጳሳትና ፶፯ ጳጳሳት የተገኙ ሲኾን ለሙሶሊኒ በአንድ ድምፅ መልእክት አስተላልፈዋል፤ መልእክቱም እንዲኽ ይላል፡- "የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በእርስዎ መንግሥት የጠነከረችና ኃያል ለኾነች ለእናታችን ኢጣልያ ዕድገት ወደፊትም የበለጠ እንድታድግ አዘውትራ ትጸልያለች።"[67]

ሙሶሊኒ ወደ ኢትዮጵያ የሚዘምተውን የወታደር ኃይልና ባንዲራቸውን ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ እንዲባርኩ የተቻለውን ያኽል ጥረት አድርጎ ነበር። ፖፑ ምንም እንኳ እርሳቸው ራሳቸው ይኽን ባያደርጉም፣ በመላ ኢጣልያ የነበሩትን ካርዲናሎች፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ኼደውና በፋሺስት ኢጣልያ መድረክ ላይ ቆመው ኢትዮጵያን ለመውጋት

[62]Binchy, *Op. cit.*, pp. 647-648. Binchy thinks that the Pope "as the king's next door neighbour" could not do otherwise.
[63]Teeling, *Op. cit.*, p. 107. Baker, *Op. cit.*, p. 290.
[64]*Giustizia e Liberta*, May 15, 1936, quoted in Binchy, *Op. cit.*, p. 650
[65]McLeish and Grubb, "Situation on Missions in Ethiopia." See also Barker, *Op. cit.*, p. 68. Sturzo, *Op. cit.*, p. 503.
[66]Salvemini, *Op. cit.*, pp. 191-192.
[67]ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ ፻፺፱።

የሚዘምተውን ወታደር ከማደፋፈርና ከመባረክ እንዲቆጠቡ ምንም አላደረጉም፡፡[68] Osservatore Romano የተባለ የቫቲካን ልሳን የኾነው ጋዜጣ የኢጣልያ ጳጳሳት ያን ለማድረጋቸው የሚከተለውን አገላለጽና ምክንያት ለመስጠት ሞክሯል፡-

> አንዲት ክርስቲያን እናት ወደ ሩቅና አደገኛ አገር የሚኼድ ልጇን እንደምትመርቅ፣ እንዲኹ ቤተ ክርስቲያንም ለጦርነት ለሚኼዱ ልጆቿ ጸሎቷንና ለነፍሳቸውና ለሥጋቸው ዕረፍትን እንዲያገኙ ምርቃቷን ትሰጣለች፡፡ ይኽን በመጥፎ ትርጒም የሚተረጒሙ ዕውቀት የሌላቸውና ደካማ ፈቃድ ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡[69] ብሏል፡፡

የኢጣልያ ካርዲናሎች፣ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት ኢትዮጵያን ለመውረር የሚኼዱትን ወታደሮችና ባንዲራቸውን መባረክ ብቻ ሳይኾን፣ ለጦርነቱ ወኔ የሚቀሰቅሱ ንግግሮችንም አድርገዋል፡፡ ከዚኽም ባሻገር በኢትዮጵያ ላይ የሚደረገው ጦርነት ትክክለኛና ተገቢ ጦርነት መኾኑን የሚገልጥ በራሪ ደብዳቤዎችን ጽፈዋል፡፡ እንደዚኹም በኢጣልያ ላይ ማዕቀብ የጣሉትን የመንግሥታቱን ማኅበር በተለይም የታላቋ ብሪታንያን መንግሥት በመንቀፍ ደብዳቤ አሠራጭተዋል፡፡[70]

በግልጽ የኢጣልያ ካርዲናሎች፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት የኢጣልያ ኢትዮጵያን መውረርና ማሸነፍ በሀገሪቷ የካቶሊክ ሚስዮን መስፋፋት እንደኾነ አበክረው ተመልክተውታል፡፡[71] የሚላኖ ሊቀ ጳጳስ ካርዲናል ሞንሲኞር ሹስተር እ.ኤ.አ. ጥቅምት ፳፰ ቀን ፲፱፻፴፭ ዓ. ም. በአንድ ክብረ በዐል ላይ ንግግር ሲያደርግ የዚኽ በዐል አከባበር የፖሊቲካ በዐል አከባበር አይደለም፡፡ ይኽ ትልቅ የሃይማኖት በዐል ነው፡፡ አድማጮቹንም በሙሉ ልብ እንዲተባበሩ እንዲኽ ሲል አሳሰባቸዋል፡- "በዚህ ብሔራዊና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥራ በተለይ በአኹኑ ጊዜ የኢጣልያ ወታደሮች የክርስቶስን መስቀል ይዘው በድል አድራጊነት ሲጓዙ የባርነትን ሰንሰለት ይበጣጥሳሉ፤ ለወንጌል ሚስዮናውያንም መንገዱን ኹሉ ክፍት አድርገዋል …፡፡"[72]

የኢጣልያ ወታደሮችን ከፍ ከፍ በማድረግ እንዲኽ አለ፡- "ጀግናው ወታደር የአባቱን ትእዛዝ ያለ ፍርሐት በመታዘዝ የኢትዮጵያን በር ለካቶሊክ እምነትና ለሮማውያን ሥልጣኔ ክፍት እያደረገ ነው፡፡"[73]

---

[68]Teeling, *Op. cit.*, p. 129. Jemolo, *Op. cit.*, p. 260.
[69]*Osservatore Romano,* October. 25, 1935. Cf. Salvemini, *Op. cit.*, p. 192.
[70]The Tablet, February. 24, 1936, p. 7. Salvemini, *Op. cit.*, p. 192. Manchester Guardian, February 24.
[71]*The Tablet*, July 4, 1936, p.7.
[72]*The people d'Italia*, October. 29, 1935.
[73]*People d'Italia,* October. 29, 1935.

እንደገና ካርዲናል ሹስተር የሮም ጉዞ ፲፮ኛው ክብረ በዐል ላይ ሲናገር ጉዞውን እንዲኽ ሲል ያሞግሳል፡- "ይኽ ጉዞ ኢትዮጵያን ከባርነትና ከመናፍቅነት ለማዳን ነፍሳትን ያዘጋጃል፤ እንዲኹም የጥንት የሮም የክርስቲያንን ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ተሐድሶን ለማምጣት ነው፤"[74] ብሏል፡፡ ካርዲናል የፓሌርሞ ሊቀ ጳጳስ የኀደኛውን የካርዲናል ሹስተርን አርአያ በመከተል ወታደራዊ ቀስቃሽ ንግግር አድርጓል፡፡ ለሲሲልያን መድፈኞች ባንዲራ ሲቀበሉ በተደረገው በዐል ላይ ሲናገር ማዕቀብ ፀረ ክርስትና ነው፡፡ የኢጣልያ ወታደሮች ለአፍሪካ ሥልጣኔንና ክርስትናን እያመጡ ነው፡፡[75]

የብሪንዲዚ ሊቀ ጳጳስ እ.ኤ.አ. ኅዳር ፲፰ ቀን ፲፱፻፴፭ ዐ.ም. ሲናገር እንዲኽ በማለት የታላቋ ብሪታንያን መንግሥት አወገዘ፡- "የታላቋ ብሪታንያ ራስ ወዳድ ሥራ ኢጣልያን ለመጉዳትና ያልሠለጠነና የባሪያ ገዢ የኾነውን ከኢጣልያ አራት እጥፍ የሚያኽል ሕዝብ የሌለበትን ሀገር የሚገዛ ንጉሥን ለመደገፍ የታቀደ ነው፡፡"[76] ሲል ተናግሯል፡፡ የኖቼራ ኡምብራ ጳጳስ ለሀገረ ስብከቱ በጻፈው ሰርኩላር ደብዳቤ በኢትዮጵያ ላይ የሚደረገው ጦርነት ትክክለኛና ቅዱስ ጦርነት መኾኑን ገልጿል፡፡[77] እንደዚኹ የታራንቶ ሊቀ ጳጳስ እ.ኤ.አ. የካቲት ፳፫ ቀን ፲፱፻፴፮ ዐ.ም. በአደረገው ንግግር የፋሺስት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያደረገው ወረራ ትክክለኛ መኾኑን እንዲኽ ሲል ገልጾታል፡-"የኢጣልያ ድል የመናፍቃንና የአሕዛብ ሀገር የኾነችውን ኢትዮጵያን ለካቶሊክ እምነት መስፋፋት ክፍት አድርጓታል፡፡ ስለዚኽ በኢትዮጵያ ላይ የሚደረገው ጦርነት ተገቢና ቅዱስ ጦርነት ነው፤ እንደውም የመስቀል ጦርነት ነው፡፡"[78] ብሏል፡፡

ከኢጣልያን ካህናት ሥራዎች እጅግ የሚያስገርመው የተቀደሱትን የቤተ ክርስቲያን የወርቅና የብር ዕቃዎችን ኢጣልያ በጦርነቱ ምክንያት የነበረባትን የገንዘብ ችግር እንድትወጣበት ለፋሺስት ባለሥልጣኖች መስጠታቸው ነበር፡፡[79] A. C. Jemolo ሲጽፍ በአንድ በተለየ "የእምነት ቀን በዐል" ካህናቱና ምእመናኑ በቅንዓት ተነሣሥተው "ቀድሞ በስእለት የተሰጡትን የየአብያተ ክርስቲያናቱን ወርቅና ብር ሰብስበው ለኢጣልያ መንግሥት አስረከቡ፤"[80] የNew Times and Ethiopia News አዘጋጅ የኢጣልያ ካህናት "የወርቅ መስቀሎቻቸውን ሸጠው የኢትዮጵያን ክርስቲያኖች ለመጨረስ የሚያገለግል የጦር መሣሪያዎችን ለመግዣ እንዲኾን ገንዘቡን ለኢጣልያ ግምጃ ቤት ገቢ

[74]Ibid, October. 29, 1936. Cf. *The Tablet,* November. 7, 1936.
[75]*PRO,* FO 371, 20179, Montgomery of the British Legation in the Vatican to Foreign Office, Rome, January.10, 1936.
[76]Salvemini, *Op. cit.,* 192-193. Cf. *New Times and Ethiopia News,* October. 3, 1936.
[77]Binchy, *Op. cit.*, p. 678.
[78]*New Times and Ethiopia News,* October. 3, 1936. See also Salvemini, *Op. cit.,* p. 193.
[79]Salvemini, *Op. cit.,* p. 193. Jemolo, *Op. cit.*, p. 260.
[80]Jemolo, *Op. cit.,* p. 260.

በማድረጋቸው"[81] በጥብቅ አውግዟቸዋል፡፡ የሲቪልታ ካስቴላኒ ጳጳስ እ.ኤ.አ. ታኅሣሥ ፰ ቀን ፲፱፻፴፭ ዐ.ም. በሙሶሎኒ ፊት ንግግር ሲያደርግ "ይኽንን የጀግኖች ታላቅነት ቀን እንዳይ ስለፈቀደልኝ ልዑል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ"[82] በማለት በሙሶሊኒ ፊት ቀርቦ የወርቅ መስቀሉንና የወርቅ ሐብሉን ከአንገቱ አውልቆ የፋሺስትን ሰላምታ በመስጠት ለሙሶሊኒ ሰጠው::

ከዚኽ በኋላ የሳን ሚኒያቶ ጳጳስ ተነሥቶ ለዱቼ ሙሶሊኒ "ለኢጣልያ ድል የኢጣልያ ካህናት የአብያተ ክርስቲያናትን ወርቅ ኹሉንም የደወሎቹን ነሐሶች አቅልጠን ለመስጠት ዝግጁዎች ነን፤"[83] ብሎ ዐወጀ፡፡ ከዚኽም በላይ በጣም የበዙ የኢጣልያ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት የጽጽስና የወርቅ ቀለበቶቻቸውንና የጽጽስና የወርቅ መስቀሎቻቸውን ከነ ሐብሉ እያወለቁ የሀገር ወዳድነት ምልክት እንዲሆንላቸውና ፋሺስቱ ሙሶሊኒ በኢትዮጵያ ላይ የሚያካኺደውን ጦርነት በመደገፍ ለፋሺስት ባለሥልጣኖች ሰጥተዋል፡፡[84] (*The Tablet* የተባለው መጽሔት "ቫቲካን በመሐል ገብቶ ጳጳሳት የጽጽስና መስቀላቸውን እያወለቁ ለመንግሥት እንዳይሰጡ ብሎ አዟል፤" ብሎ የጻፈው ዘገባ እውነተኛነቱ አልተረጋገጠም::[85])

አንድ ሰው ከዚኽ የሚከተለውን ሊጠይቅ ይችላል፡- "በዚኽ ጦርነት ውስጥ ጣልቃ አልገባም ገለልተኛ ነኝ" የሚሉት ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ ካህናቱ (ካርዲናሎቹ፣ ሊቃነ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ) ጦርነቱን በመደገፍ ከመናገርና ሀገር-ወዳድነታቸውን በይፋ ከመግለጥ እንዲቆጠቡ ለምን አላዘዟቸውም? እንደሚታወቀው ፖፑ የዓለም-አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊ ከመሆናቸውም በላይ በተለይ የኢጣልያ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ኃላፊ ናቸው፡፡ ቢንቺ እንደሚለው በዚኽ ኹኔታ የፖፑ አስተዳደራዊ ግንኙነቱ ከኢጣልያ ቤተ ክርስቲያንና ከጳጳሳቱ ጋር በተግባር ብቻ ሳይኾን በቤተ ክርስቲያንም ሕግ መሠረት እጅግ የቀረበና የላቀ ነው፡፡ ስለዚኽ ፖፑ "በኢጣልያ ካርዲናሎች፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ላይ ከሌሎቹ ይልቅ የበለጠ ሥልጣን አላቸው::"[86] ፖፑ ከፈለጉ በጥሩ ውጤት በመካከላቸው ገብተው ሊቆጣጠሯቸውና ቢያንስ በግል ደረጃ እንደዚኽ ካለ የጦርነት ፕሮፓጋንዳ ውስጥ እንዳይገቡ የኢጣልያንን ካርዲናሎች፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ሊመክሯቸው ይችሉ ነበር፡፡ በርግጥ እንደ ሚመስለው የእሳቸው ጣልቃ አለመግባትና የኢጣልያንን ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖችን አድራጎት በዝምታ ማለፍ በነገሩ የተስማሙበት መኾኑን በግልጥ ያመለክታል፡፡ ስለዚኽ ነበር ብዙ ሰዎች ፖፕ ፒዮስ ፲፩ኛ የፋሺስት

[81]*New Times and Ethiopia News,* January. 30, 1937, p. 3.

[82]Salvemini*, Op. cit.*, p. 193. *New Times and Ethiopia News,* October. 17, 1936.

[83]Binchy, *Op. cit.*, p. 678. See also Salvemini, *Op. cit.*, p. 193.

[84]Binchy, *Op. cit.*, p. 678.

[85]*The Tablet,* July 4, 1936, p. 7.

[86]Binchy, *Op. cit.,* p. 645.

መሪዎችን ያደፋፍሩ እንደ ነበርና የፋሺስትን መርሖ ይደግፉ ነበር እያሉ የሚከሱት። የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ለጦርነት የሚገፋፉ የትምክህተኝነት ንግግር ሲያደርጉ ፖፑ ምንም አልተናገሯቸውም።[87]

ኢጣልያ ኢትዮጵያን እንደ ወረረች ቫቲካን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ በበለጠ እንድትስፋፋ በብዙ መቶ የሚቈጠሩ ካህናትንና ሲስተሮችን በመላክ የተቻላቸውን ኹሉ አድርገዋል። ከዚኽ ቀጥሎ ያለው ዘገባ እንደሚገልጸው፡-

> ከጥቂት ጊዜ ጀምሮ ቫቲካን በቅርብ ጊዜ ለምትሸነፈው ኢትዮጵያ የሚዘጋጁ ቊጥራቸው የበዛ ቀሳውስትን ታሠለጥን ነበር ... ፩፻ የሚኾኑ ቀሳውስት እየሠለጠኑ ነበር። እነዚኽም የኢጣልያ የግዛት ሥልጣን በኢትዮጵያ እውነት በሚሆንበት ጊዜ በሀገሩ ኹሉ ለመሠራጨት ዝግጁዎች ነበሩ።[88]

እ.ኤ.አ. መስከረም ፲፱፻፴፮ ዐ.ም. የኢጣልያ ወታደሮች አዲስ አበባን በያዙ በጥቂት ወራት ውስጥ ቫቲካን የሮዶስ ሊቀ ጳጳስን ሞንሲኞር ካስቴላኒን የአፖስቶሊክ ጎብኚ አድርጋ ወደ ኢትዮጵያ ላከች። እኚኽ ሊቀ ጳጳስ የተላኩትም "በቦታው ላይ ኾነው የሕዝቡን መንፈሳዊ ችግሮች ለማጥናትና በአዲሱ የኢጣልያ አስተዳደር ተግባራዊ የሚሆን ፕሮግራም ለመቀየስ ነበር።"[89] ሲመለሱ ሊቀ ጳጳስ ካስቴላኒ ብዙዎች ካርዲናሎች በተገኙበት የፕሮፓጋንዳ ፊዴ ጸሐፊና የቫቲካን ከተማ ገዥ በተገኙበት ንግግር አደረጉ። ከተናገሯቸውም ውስጥ የሚከተለው ይገኝበታል፡-

> ለሚስዮን ሥራ አኹን እውነተኛ ነፃነት፣ ትልቅ ሰላም እንዲሁም ውብ የኾነ ድል ተገኝቷል። አኹን ኢትዮጵያ በትልቅ ተስፋ ለተቀደሰ ትንቢት አይኖቿን ወደ ሰማይ አንሥታለች። ይህ ደግሞ እየመጣ ነው። ምክንያቱም ይኽ በጌታ የተወሰነ ነው። ለሀገሪቷ ወንጌልን ለመሰበክ በአንዳንድ እንቅፋቶች ተሰናክለው ቀርተው ነበር ... አሁን የሆነው ለውጥ ግን ተስፋችንን እውን ያደርገዋል።[90]

አኹን ተስማሚ በኾነው የፖሊቲካ ለውጥ ምክንያት ቫቲካን የነበሩትን ሚስዮኖችና የቤተ ክርስቲያን መዋቅር በአፋጣኝ በዐዲስ መልክ እንደገና እንዲደራጁ አደረገች። እ.አ.አ. ፲፱፻፴፮ ዐ.ም. መጀመሪያ ላይ ፖፑ ዐዲስ ልዩ ኮሚሽን አቋቋሙ። የኮሚሽኑም አባላት የኦርየንታል ቤተ ክርስቲያን ማኅበር፣ የፕሮፓጋንዳ ፊዴ ማኅበርና የExtraordinary

[87] Ibid, p. 643. Baer, *Op. cit.* p. 288. Salvemini, *Op. cit.*, pp. 193-194.
[88] Rome, *Op. cit.*, p. 81. However, Rome does not give the source of his information.
[89] ቃለ መጠይቅ የተሰጠው በካርዲናል ቲሴራንት *in Gazetta del Popolo*, October. 22, 1936.
[90] *New Times and Ethiopia News,* February. 13, 1937, p. 7. See also *Osservatore Romano,* January 23, 1937..

Affairs ማኅበር ተወካዮች ነበሩ፡፡ ይኽ ኮሚሽን የተሠየመው በቅርቡ በኾነው የፖሊቲካ ለውጥ መሠረት በኢትዮጵያ የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን እምነትና ተግባር እንዴት ማስፋፋት እንደሚቻል ለማጥናት ነበር፡፡[91] የኮሚሽኑ ጥናቶች ለፖፑ ቀርቦ በዚሁ መሠረት የቤተ ክርስቲያኑ ዐዲስ አደረጃጀት ተከናወነ፡፡ ኹለቱ የቫቲካን ታላላቁ ማኅበሮች በኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ሕዝቦችን ወደ ካቶሊክ እምነት እንዲ መልሱ ሓላፊነት ተሰጣቸው፡፡ እነዚኽም የፕሮፓጋንዳ ፊዴ ማኅበር በተለይ ክርስትና ላልተሰበከባቸው አረማውያን ለሚበዙበት ሀገር ሲኾን፣ የኦርየንታል ቤተ ክርስቲያን ማኅበር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መካከል እንዲሠሩ ተወሰነ፡፡[92]

እ.ኤ.አ. መጋቢት ፳፫ ቀን ፲፱፻፴፯ ዐ.ም. በወጣው ትእዛዝ መሠረት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተቋም በኢትዮጵያ እንደገና እንዲደራጅ ታወጀ፡፡ በዚኽ ዐዋጅ መሠረት የቀድሞው የአቢሲንያ አፖስቶሊክ ቪካሪያቴ ተሰረዘ፡፡ በዚኽ ፈንታ ሌሎች ብዙ ቪካሪያቴዎች (አህጉረ ስብከቶች) እና ፕሪፌክቱሬዎች (ንኡሳን አህጉረ ስብከቶች) ተቋቋሙ፡፡ ይኽም የኾነው በዐዲሱ የኢጣልያ የፖሊቲካ አከፋፈል መሠረት ነበር፡፡ በዚኹ መሠረት ዐዲሱ የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በስድስት አፖስቶሊክ ቪካሪያቴ (አህጉረ ስብከቶች) እና በአራት አፖስቶሊክ ፕሪፌክቱሬዎች ተከፋፈለ፡፡

## ፬. ማጠቃለያ

በሰነድ እንደተረጋገጠው በጊዜው በሥልጣን ላይ የነበሩት ፖፑ ፒዮስ ፲፩ኛ ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በምትወርርበት ጊዜ መደሰታቸው የአደባባይ ምስጢር ነበር፡፡ ፖፑ ፒዮስ ፲፩ኛ እ.ኤ.አ ሰኔ ፲፫ ቀን ፲፱፻፴፫ ዐ.ም. አብዛኞቹ ለመዋጋት ወደ ኢትዮጵያ ለሚኼዱት ፸፻ ለሚኾኑ የቀድሞ ወታደሮች ንግግር ማድረጋቸውና ቅዳሴ መቀደሳቸው፣ እንዲኹም መስከረም ፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዐ.ም. ፲፫፻ የሚኾኑ የቀድሞ ወታደሮችን ተቀብለው ማነጋገራቸውና መምከራቸው ሙሶሊኒ በኢትዮጵያ ላይ ለሚያደርገው ጦርነት የሞራል ድጋፍ ለመስጠት ነበር፡፡ ስለዚኽ ቫቲካን ፩ኛ. ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ስትወርር ምስጢራዊ የኾነ የሞራል ድጋፍ በመስጠቷ፣ ፪ኛ. የኢጣልያ ወታደሮች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እንደዚያ ያለ የጭካኔ ጭፍጨፋ ሲያደርጉ ዐለሙ ኹሉ ሲጮኽ ቫቲካን ምንም ድምፅ ባለማሰማቷ፣ ፫ኛ. የፋሺስቱ የኢጣልያ ወታደሮች ኢትዮጵያን በመርዝ ጋዝ እየረጩ በመፍጀት ባሸነፉ ጊዜ ፖፑ ይኽን ድል የሚያስደስት ድል ብለው በመናገራቸው፣ ፬ኛ. የፋሺስት ጭፍሮች ከ፳፻ የሚበልጡ አብያተ ክርስቲያናትንና ገዳማትን ሲያቃጥሉ፣ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የደብረ ሊባኖስ፣ ዜና ማርቆስና ዝቋላ

[91] *The Tablet,* May 29, 1937, p. 771; July 17, 1937, p. 83. *Fide News Service,* July 10, 1937, p. 162.

[92] *Fide News Service,* July 10, 1937, pp. 162-163. Cf. Interview given by Cardinal Tisserant, *in Gazetta del Popolo*, October 22, 1936.

መነኰሳትንና ካህናትን እንዲኹም ጳጳሳትን (አቡነ ጴጥሮስንና አቡነ ሚካኤልን) በግፍ ሲገደሉ ቫቲካን ዝም ብላ ትመለከት ነበር።

ናዚ ጀርመን ፮ ሚሊዮን የሚኾኑ አይሁዶችን በጨፈጨፈች ጊዜ ቫቲካን ምንም ነገር ሳትናገር በመቅረቷ በኋላ ተፀፅታ አይሁዶችንና የእስራኤልን መንግሥት በተደጋጋሚ በይፋ ይቅርታ ጠይቃለች። በኢትዮጵያ ላይ በፈጸመችው በደል ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ አልጠየቀችም።

በኢጣልያ ወረራ ጊዜ በበዙ ሺ የሚቆጠሩ የቤተ ክርስቲያን ንብረቶችና ብርቅዬ የብራና መጻሕፍት ተዘርፈው በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር ውስጥ ይገኛሉ። ቫቲካን እነዚኽን ክቡራት ዕቃዎችና መጻሕፍት ለባለቤቷ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለመመለስ ፈቃደኛ ስትኾን አይታይም።

በኢትዮጵያ ሕዝብና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተፈጸመውን ግፍና በደል በጽሞና ተመልክተው፣ አንደኛ የኢትዮጵያ መንግሥት፣ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ በተለይ ብፁዓን የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ጽ/ቤት እንዲኹም ማኅበረ ቅዱሳን በተለይም ወጣቱ ትውልድ ቫቲካን በኢትዮጵያ ሕዝብና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ በፈጸመችው በደል የኢትዮጵያን ሕዝብና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ይቅርታ እንድትጠይቅ፤ ኹለተኛ ከኢትዮጵያ ተዘርፎ በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር የተቀመጡትን ብርቅዬ የብራና መጻሕፍትንና የቤተ ክርስቲያን ንብረቶችን ቫቲካን እንድትመልስ ያላሠለሰ ጥረትና ተፅዕኖ ማድረግ ይገባቸዋል።